# ከኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል

## ጋር በመተባበር በየሳምንቱ የሚታተም

# ተቋማዊ ትልምና ትግበራ

የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል በአጭርና በመካከለኛ ጊዜ ዕቅዱ ሀገራዊ የኃይል ፍላጎትን ለማሳካት በረጅም ጊዜ ዕቅዱ ደግሞ የአፍሪካን በተለይም የምሥራቅ አፍሪካን ሕዝቦች በኃይል አቅርቦት ለማስተሳሰር ራዕይ ሠንቆ እየሠራ መሆኑን የተቋሙ የፕላኒንግ ዘርፉ ሥራ አስፈጻሚ አቶ አንዷለም ሲዓ ይገልጻሉ። ዘርፉ ተቋማዊ ትልሙን እውን ማድረግ የሚያስችሉትን የተለያዩ የአሠራር ሥርዓቶች ቀይሷል። በተለይ ዘመኑ ከደረሰባቸው ቴክኖሎጂዎች ጋር እያጣጣሙ ማቀድና መተግበር ወይም ቀደም ሲል የነበረውን ተለምዷዊ አሠራር ወደ ዘመናዊ የአሠራር ሥርዓት ማሸጋገር ዘርፉ እየተከተላቸው ካሉ የለውጥ ሥራዎች መካከል የሚጠቀሱ ናቸው።

ተቋሙ ለኤሌክትሪክ ኃይል ማመንጫነት የሚውሉ የሀገሪቱን ኃብቶች በጂኦስፓሻል መረጃ ታግዞ የት ቦታ እንደሚገኙ፣ በምን መጠን እንዳሉ፣ ለምን ዓይነት ዓላማ እንደሚውሉ እና እንዴት ጥቅም ላይ መዋል እንደሚችሉ ወዘተ መረጃዎችን በሳተላይት፣ ወይም በድሮን ቴክኖሎጂ አማካኝነት ሰብስቦ ለውሳኔ ሰጪ፣ ለፖሊሲ አውጪ እና ለተጠቃሚ አካላት ያቀርባል። በመሆኑም ዘርፉ የጀመረውን ዘመናዊ የአሠራር ሥርዓት ይበልጥ ለማሳደግ ከኢትዮጵያ ስፔስ ሳይንስ እና ከጂኦስፓሻል ኢንስቲትዩት፣ ከኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት ጋር እንዲሁም ለዘርፉ ሥራ አጋዥ የሆኑ ሶፍትዌሮችን ከሚያበለጽገውና Esri እየተባለ ከሚጠራው የአሜሪካ ኩባንያ ጋር የትብብር ስምምነት አድርጓል።

ዓለም በዲጂታል ትራንስፎርሜሽን፣ ቴክኖሎጂ እና ኢኖቬሽን ፈጣን እድገት እያሳየች መምጣቱን



አቶ አንዷለም ሲዓ

ተከትሎ የውሳኔ አሰጣጥ ሂደቶች በእጅጉ እየተሻሻሉ መጥተዋል ያሉት ሥራ አስፈፃሚው፤ የጂኦስፓሻል መረጃዎችን መጠቀም ከውሰን ማስከበር ጋር ተያይዞ ያለውን ብልሹ አሠራር እና ተገቢ ያልሆነ ጥቅም ለማግኘት የሚደረገውን ሙከራ ያስቀራል። እንዲሁም የአየር ካርታዎችን በመሥራት ግንባታዎች ከመጀመራቸው በፊት እና ከተገነቡ በኋላ ያለውን ገጽታ ለማመሳከርም ይጠቅማል ብለዋል።

ሥራ ክፍሉ እንደ አዲስ ከተደራጀ በኋላ አበረታች ውጤቶች ተመዝግበዋል። በተለይም ተቋሙ የዛሬ ሦስት ዓመት ምን እንሠራለን? የአስር ዓመት ግባችን ምንድን ነው? እንዲሁም የዛሬ 25 ዓመት በምን ዓይነት ደረጃ ላይ መድረስ ይገባናል? የሚለውን በዕቅዱ አስቀድሞ አመላክቷል።

እንደ ተቋም ከዚህ በፊት በፕላኒንግ ዘርፍ ብቻ ተግባራዊ ሲደረግ የነበረውን የዕቅድ አሠራር በማስቀረት፣ ሁሉም ባለድርሻና አጋር አካላት ባለቤትና ተሳታፊ የሆኑበትን እቅድ በማፅደቅ፣ ሰነዱን ሰንዶ በሥርዓት የማስቀመጥ እና ለሚቀጥለው ትውልድ እንዲተላለፍ የማድረግ ሥራ ተሠርቷል።

የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል የሀገሪቱን የኃይል ኃብቶች በማልማት የሀገሪቱን ሕዝቦች በሚቀጥሉት አሥር ዓመታት ሙሉ ለሙሉ የኤሌክትሪክ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ማስቻል ከዋና ዋና ዕቅዶች ውስጥ አንዱ ነው። በመሆኑም የሀገሪቱን ኃይል ፍላጎት በሚመልስ መልኩ የኃይል ማመንጫዎችና ማከፋፈያ ጣቢያዎችን፣ ማስተላለፊያ መስመሮችን በመገንባትና በማስፋፋት አስተማማኝ የኃይል አቅርቦት እንዲኖር ማስቻል በዕቅዱ የተመላከቱ ዋና ጉዳዮች ናቸው። በሀገራቱ ያሉትን ፀጋዎች ተጠቅሞ አስተማማኝ የኃይል ምርትን ማሳደግና ለጎረቤት ሀገራት መሸጥ፤ በሚገኘው የውጭ ምንዛሪ የሕዝብ ተጠቃሚነትን ለማረጋገጥ ያለመ ነው። ከዚህ አንጻር በሚቀጥሉት ሁለት እና ሦስት ዓመታት የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ከየትኛውም የመንግሥት ተቋም በተሻለ የውጭ ምንዛሪ በማስገኘት በኩል ግንባር ቀደም የሚያደርገውን ዕቅድ ነድፎ ተግባራዊ በማድረግ ላይ ይገኛል።

እ.ኤ.አ. በ2020 አራት ሺ 200 የነበረውን ሀገራዊ የኃይል ምርት እ.ኤ.አ በ2030 በአራት እጥፍ በማሳደግ 17 ሺ ሜጋ ዋት ማድረስ ነው። ከኢነርጂ ተጠቃሚነት አንጻርም 15 ሺ ሜጋ ዋት ሰዓት የነበረውን ወደ 65 ሺ ሜጋ ዋት ሰዓት ማድረስ በተቋሙ የታሰቡ ትልሞች ናቸው።

በዕቅዱ የተመላከተው ሌላኛው ተግባር በዘርፉ የሀገር ውስጥና የውጭ ባለኃብቶችን በኤሌክትሪክ መሠረተ ልማት ዘርፍ ማሳተፍ የሚለው ነው። ለዚህም ሥራ ያመቸ ዘንድ የግሉ ዘርፍ በቀላሉ የሚሳተፍበትን የኤሌክትሪክ አማራጮችን በጥናት በመለየት የተለያዩ የሕግ ማሻሻያ ሥራዎች ተከናውነዋል። ይህን ተከትሎ በዘርፉ መሳተፍ የሚፈልጉ አልሚዎችም ከወዲሁ ጥያቄ እያቀረቡ መሆኑን አቶ አንዷለም ተናግረዋል። በንፋስና በፀሐይ ኃይል የማመንጨት ሥራ ላይ የግሉ ዘርፍ ጎልቶ የሚወጣበት አዲስ ዘመን እየመጣ መሆኑ ታምኖበታል።

ለዕቅድ ዝግጅት መረጃዎች ወሳኝ መሆናቸውን ያወሱት አቶ አንዷለም፤ ቀደም ሲል የተቋሙ መረጃዎች የሚሰፍሩት በወረቀት ላይ በመሆኑ ሠራተኞችም ሆኑ አመራሮች ሥራቸውን በሚለቁበት ጊዜ የሚያስፈልገውን መረጃ ለማግኘት አዳጋች እንደነበር ገልጸዋል። ይህም በአንዳንድ ጉዳዮች ላይ የመረጃ መጣረስ (መዛባት) እንዲከሰት ያደርግ ነበር። አሁን ግን ተቋሙ የዳታ ፖሊሲ በማውጣት ከወረቀት መር አሠራር ተላቆ ወደ ኮምፒዩተር በመሸጋገሩ የመረጃ አሰጣጥ ግድፈቶች እየተወገዱ መምጣታቸውን ተናግረዋል።

ከጊዜ ወደጊዜ የተቋሙ አፈፃፀም እየተሻሻለ መምጣቱን የጠቆሙት ሥራ አስፈፃሚው ለዚህም ምክንያቶቹ እያንዳንዱ ተግባር ከረጅም ጊዜ ዕቅድ ተቀድቶ የዓመት፣ የወርና የዕለት በሚል ተለይቶ ተግባራዊ የሚደረግ በመሆኑ፣ የተጠናከረ አፈፃፀምና ክትትል ስለሚደረግ እና ዕቅዱ በሚዛናዊ ውጤት ተኮር ሥርዓት ስለሚመራ እንደሆነ ጠቅሰዋል።

የተጀመረው ለውጥ ቀጣይነት እንዲኖረው የመሥሪያ ቤቱ ባልደረቦች በሙሉ ዕቅዶችን ከማስፈጸም አንጻር የየራሳቸውን ሚና መጫወት፤ የባለቤትነት ስሜትን መላበስ፤ ለተቋሙ አቅም የሚፈጥሩ ሀሳቦችን፣ እውቀቶችን እና ማቴሪያሎችን ወደ ጥቅም እንዲቀየሩ ማድረግ፤ ለሙያቸው ታማኝ ሆነው ኃላፊነትን መወጣት እንደሚገባቸው አቶ አንዷለም መልዕክት አስተላልፈዋል።

የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል